# ዛሬ እንኳን ኢስላምን አትቀበልምን?

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ

ምስጋና ለአለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ይገባው የእርሱ ርህራሄና ሰላም ለነብዩ ሙሐመድ እና ባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን።

በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ኢስላምን ከሌሎች እምነቶች ለየት ሚያረጉትን ነገሮች በአጭሩ ለምርምር እና ጥናት ቁልፍ እንዲሆን በማሰብ አዘጋጅቻለሁ፡፡ ከኢስላም ውጭ ፍትሐዊ ሆነው እውነትን ለሚፈልጉ ሰዎች ሰበብ ትሆን ዘንድ ከታች ባሉት መስፈርቶች መሰረት አውቀው ኢስላምን እንዲቀላቀሉ በማሰብ አጠር ባለ ሁኔታ ለማዘጋጀት ሞከርኩ።

- **<u>ንያቸው ስህተትን ማሳደድ ሳይሆን እውነትን መፈለግ ስለእውነት ማወቅ</u>**

በርግጥም አላህ(ሱ.ወ) እውነትን ማወቅ ለሚፈልጉ ሰወች ቀጥተኛውን ጎዳና ለመምራት ቃል ገብቶላቸዋል። እንዲሁም የኢማንን ጥፍጥና የሚያገኙበትን መንገድ ልቦናውን በመክፈት ከአላህ ጋር ሚገናኙበትን መንገድ በማግራት አላህ ያግዘዋል።

فَمَن يُرِدِ اللَّهُ أَن يَهْدِيَهُ يَشْرَحْ صَدْرَهُ لِلْإِسْلَامِ ۖ وَمَن يُرِدْ أَن يُضِلَّهُ يَجْعَلْ صَدْرَهُ ضَيِّقًا حَرَجًا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِي السَّمَاءِ ۚ كَذَٰلِكَ يَجْعَلُ اللَّهُ الرِّجْسَ عَلَى الَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ

[ ٦:١٢٥]

‹‹አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን (ልቡን) ለኢስላም ይከፍትለታል፡፡ ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ቺጋራ ወደ ሰማይ ለመውጣት አንደሚታገል ያደርገዋል፡፡ እንደዚሁ አላህ በእነዚያ በማያምኑት ላይ ርክሰትን ያደርጋል፡፡››

- **<u>ወደ አላህ ብቻ እውነተኛ ፀሎት ማድረግ እውነትን እንዲያሳውቀው እና እንዲያድለው ችክ ማለት።</u>**

كَانَ النَّاسُ أُمَّةً وَاحِدَةً فَبَعَثَ اللَّهُ النَّبِيِّينَ مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ وَأَنزَلَ مَعَهُمُ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ لِيَحْكُمَ بَيْنَ النَّاسِ فِيمَا اخْتَلَفُوا فِيهِ ۚ وَمَا اخْتَلَفَ فِيهِ إِلَّا الَّذِينَ أُوتُوهُ مِن بَعْدِ مَا جَاءَتْهُمُ الْبَيِّنَاتُ بَغْيًا بَيْنَهُمْ ۖ فَهَدَى اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا لِمَا اخْتَلَفُوا فِيهِ مِنَ الْحَقِّ بِإِذْنِهِ ۗ وَاللَّهُ يَهْدِي مَن يَشَاءُ إِلَىٰ صِرَاطٍ مُّسْتَقِيمٍ [٢:٢١٣]

‹‹ ሰዎቹ ሁሉ አንድ ሕዝብ ነበሩ፤ (ተለያዩ)፡፡ አላህም ነቢያትን አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች አድርጎ ላከ፡፡ ከእነርሱም ጋር መጻሕፍትን በሰዎቹ መካከል በዚያ በርሱ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ በእውነት አወረደ፡ ፡ በእርሱም (በሃይማኖት) ግልጽ አስረጂዎች ከመጡላቸው በኋላ በመካከላቸው ለኾነው ምቀኝነት እነዚያው የተሰጡት እንጂ አልተለያዩበትም፡፡ አላህም እነዚያን ያመኑትን ሰዎች ለእዚያ ከእውነት በርሱ ለተለያዩበት በፍቃዱ መራቸው፡፡ አላህም የሚሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል፡፡»

- ***<u>የዲን ወገንተኛ አለመሆንን ጭፍን የሆነ መከተል በአባት በአያቶቻችን ዲን መፅናት ያለእውቀት መመራትን መተው፡፡</u>***

*ተመልክቶ አስተውሎ አንብቦ እና ተረድቶ በምክንያታዊነት ኢስላምን መከተል ። እንጂ በስሜት በይምሰል እንዲሁም በውርስ ዲን መከተል ከእውነታ ያረቃል ።*

وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ اتَّبِعُوا مَا أَنزَلَ اللَّهُ قَالُوا بَلْ نَتَّبِعُ مَا أَلْفَيْنَا عَلَيْهِ آبَاءَنَا ۗ أَوَلَوْ كَانَ آبَاؤُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ شَيْئًا وَلَا يَهْتَدُونَ [٢:١٧٠]

«ለእነርሱም «አላህ ያወረደውን ተከተሉ» በተባሉ ጊዜ «አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን» ይላሉ፡፡ አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና (ወደ እውነት) የማይመሩም ቢኾኑ (ይከተሉዋቸዋልን?)>>

*በአለም ላይ ያለ የአደም ልጅ ኢስላምን ሆነ የሌላ እምነት ተከታይ ስለኢስላም ለማውቅ መመርመር መጣርና መፈለግ ግዴታ ነው።ኢስልምና ለአረብ ብቻ የመጣ ሐይማኖት እንዳልሆነ የሰውልጅ በጠቅላላ ሊያውቀው ይገባል። ኢስላም ከዘረኝነት የነፃ ነው።ደሀ ቢሆን ሀብታም ጥቁር ቢሆን ነጭ በኢስላም ያመነና የተገበረ በኢስላም አመነ። የኢስላም መልክተኛ ነብዩ ሙሐመድ የዘር ሀረግ ቢሆን የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሙአዚን ቢላል ኢብኑ ረባህ የሀበሻ ባርያ ሩማዊው ሱሀይብ ፤ የፋርሱ ሰልማን ቢሆን እንኳ ኢስላምና በመካና በመዲና የተገደበ አይደለም በምድረ አረብም ቢሆን አልተገደበም ማንኛውም አገር ኢስላም ከተቋቋመበት የኢስላም አገር ትሆናለች። የአፍሪካ ደን ውስጥ ቢሆን እንኳ*

*= ኢስላም ሙሉ የሆነ እና ሽሪዐዊ ጎዳና የያዘ ሃይማኖት ነው።በግልም ይሁን በአለም አቀፍ ደረጃ ሚደረጉ ነገሮች ላይ ኢስላም ተጠያቂ አይደለም።በዚህ ሁኔታ ብዙ የሆኑ ሀገራትና አንጃወች ከኢስላም አካል እንደሆኑ ይገልጻሉ። ኢስልምና ከነሱ የጸዳ ነው።እናም ዋናውን ኢስላም ለማጠልሸት ትልቅ የሆነ አሻራ ማሳረፍ ችለዋል። በዚህ ምክንያት ከኢስላም ውጭ ያሉ አካላትን በተግባር በንግግር እና በአስተሳሰብ ከኢስላም ለማራቅ ትልቅ ጥረት አርገዋል። የተረጋጋች እና ሰላማዊ ተፈጥሮ በጠቅላላ ለኢስላም የቀረበች ናት። በተቀረ ያሉ እምነት ሁሉም ከተፈጥሮ ይጋጫሉ ።ይህን ንፁህ በሆነ ጭንቅላት ተመልከቱት። ከእስልምና ውጭ የሆኑ ነገሮችን ሙስሊሞች አይቀበሉትም። ምክንያቱም እስልምና አንድነት ነው። እስልምና ውስጥ ሁሉም ነገር ግልጽ ነው። የተፈቀዱ የተከለከሉ መልካምስራ እና አጥፊ ስራዎች፤ ጥርት ያለ እና ግልፅ ነው። ነገር ግን እኚህን ነገሮች በመያዝ ሙስሊሞች በመሀላቸው ልዩነት አለ።*

ثُمَّ أَوْرَثْنَا الْكِتَابَ الَّذِينَ اصْطَفَيْنَا مِنْ عِبَادِنَا ۖ فَمِنْهُمْ ظَالِمٌ لِّنَفْسِهِ وَمِنْهُم مُّقْتَصِدٌ وَمِنْهُمْ سَابِقٌ بِالْخَيْرَاتِ بِإِذْنِ اللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ هُوَ الْفَضْلُ الْكَبِيرُ [٣٥:٣٢]

«ከዚያም እነዚያን ከባሮቻችን የመረጥናቸውን መጽሐፉን አወረስናቸው፡፡ ከእነርሱም ነፍሱን በዳይ አልለ፡ ፡ ከእነርሱም መካከለኛ አልለ፡፡ ከእነሱም በአላህ ፈቃድ በበጎ ሥራዎች ቀዳሚ አልለ፡፡ ያ (ማውረስ)፤ እርሱ ታላቅ ችሮታ ነው፡፡»

- **<u>ከኢስልምና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን እውቀቶች በምርምር እና ጥናት መንገዶችን በመያዝ እውቀትን መፈለግ መጠየቅ ገለልተኛ እና ተፃራሪ ተቃዋሚ አለመሆን</u>**

ስለዚህ ትክክለኛ የሆነው የኢስላም ውርስ ቁርዐን እና የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር እንዲሁመም ኡለሞች የተስማሙበትን መሰረት በማድረግ  ኢስላምን ማወቅ ለፈለገ ግድ ይሆንበታል።

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት ‹‹በመሀከላችሁ ከኔ በኃላ በመስራታችሁ ማትጠፉበት የሆነ ነገር ቁርዐንና የኔን ምንገድ (ሱና) ትቼላችኃለሁ።፡››

የአደም ልጅ የተሻለ እና ሙሉነትን በዱንያዊ ጉዳዮች የጎደለውን ለመሙላት መፈለግ ሰዋዊ እና ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። ለሱ ጥሩ እና የተሻለውን አነፃፃሪ በተወሰነ ግዜ ያገኘዋል። ለሱ በላጩ እና ሙሉው ዲኑን መፈለግ ነው። ለሩሁ ደስታ ለነፍሱ ስክነት ለአካሉ  ሰላም ለንብረቱ ክብር ኢስላም ያረጋግጥለታል

ውሳኔው በእጅ ስለሆነ  በተወሰነ ግዜ እና በተረጋጋ እና አንፀባራቂ ንባብ ለውሳኔ ባለመቻኮል ጥሩና የተሻለውን ውሳኔ መወሰን የሱድሻ ነው።

የመጨረሻ ቀን እንዳለ አምኖ እውነት መሆኑን በእርግጥ ማወቅ ፦ ይህ ማለት ከሞት በኂላ ያለውን ህይወት እውነታነቱን

ይህ መፅሐፍ ያነበበን ሁሉ ልቡን እንዲ ከፍትለት እውነትን መቀበል እንዲያድለው አላህን እጠይቃለሁ፡ ፡

- **<u>ኢስላም ምን ማለት ነው</u> ?**

ኢስላም ማለት ለአላህ እጅ መስጠት መማረክ ማለት ነው። ኢስላም በጌታውና በባርያው መሀል ዘውታሪ የሆነ ትስስር ሲሆን አንድ የአላህ ባርያ ከተከለከሉ መንገዶች ተቆጥቦ ግዜ በተወሰነላቸው  በቀንና በለሊት የፈርድ ሰላቶች ላይ አምስት ግዜ ከጌታው ጋር ይገናኛል። የዕለት ተዕለት ስራዎቹም በዱዐ እና ዚክር በማድርግ ከጌታውጋ ያለውን ግኑኙነት ያጎለብታል ከምግብ በፊትና በኃላ ፤መፀዳጃ ቤት ከመግባቱ በፊት እንዲሁም በኃላ ፤ ሲተኛና ሲነሳ ፤ ከውዱዕ በፊትና በኃላ ከሚስቱጋ በሚያረገው ግንኙነት መኝኝቸ ላይ ሲወጣ ሲወርድ …ወሀተ የዉስሊም ህይወት በጠቅላላ ከጌታውጋ የተሳሰረ ነው።

## ኢስላምን ለየት ሚያረጉ ነገሮች

ከሰማይ ከወረዱ ሐይማኖቶች የመጨረሻው መሆኑ አላህ (ሱ.ወ) ከዚህ ዲን ውጭ ያሉ ዲኖችን እንድንገዛ አልወደደልንም

ይህ ዲን እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ በየትኛውም ቦታ ዘመን ለየት ማለቱ ግድ ነው። ለየት ሚያረጉት ነገሮች መሐከል

## 1-ተፈጥሯዊ ሐይማኖት ነው።

የሰዎቸ ተፈጥሮ አላህ እንዳለ እና መኖሩን ለማረጋገጥ ምቹ የሆነ አፈጣጠር ነው። ተፈጥሮን ተመልክቶ የፈጣሪን ፀጋዎች በአዕምሮ በማስተንተን የአላህን መኖር ማረጋገጥ ይቻለው ዘንደ አላህ ተፈጥሮን አግርቶለታል። ፍጥረታት በጠቅላላ አላህ በዘረጋላቸው ጎዳና ይጓዛሉ።

فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا ۚ فِطْرَتَ اللَّهِ الَّتِي فَطَرَ النَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ اللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ [٣٠:٣٠]

«ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፡፡ የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በእርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዟት)፡፡ የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፡፡ ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፡፡ ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም፡፡»

የአደም ልጅ በጠቅላላ ሀይማኖታዊ መሰረቱ ኢስላም ነው፡፡ ነገር ግን በሰው ልጅ ዙሪያ ያሉ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች በሚያሳደርባቸው ተፅእኖ ምክንያት ከትክክለኛ ጎዳና ያዘናጋቸዋል ለጥሜት ይዳረጋሉ በአላህ ላይ ያጋራሉ ከአላህ ውጭ ሌላን አካል መገዛት ይጀምራሉ፡፡ የአላህንም መኖር ያስተባብላሉ፡፡

«የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እነዳስተላለፉት አንድም አልተወለደም በእስልምና ላይ ቢሆን እንጂ አባታቸው የሁዳ ክርስቲያን መጁሳን ባያረጓቸው»

## 2- አሐዳዊነት

ኢስላም ለአንድ አምላክ አጥርቶ መገዛትን ሚያስተምር ከሱውጭ ያለን ፍጥረት እንዳንገዛ ያዘዘ ዲን ነው፡፡ በጌታውና በባርያው መሀል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖረን የሰብካል፡፡በጌታው እና በባርያው መሀል ያለ ግንኙነት ቀጥያለ ግኑኝነት እሱም በአላህ ላይ ሙሉ እምነት እና በማንኛውም ነገር ወደአላህ በመጠጋት ምህረት እገዛን በመሻት ያለማንም አማላጅነት ሁሌም በጌታውና በባሪያ ማህከል ያለን ማንኛውም እንቅፋት የጸዳል፡፡ በሰዎች እና በጌታቸው መሀል ግርዶ እያረጉ በአላህ ላይ ሲያጋሩ የነበሩ ሰዎችን ኣላህ ያነውራቸዋል፡፡

أَلَا لِلَّهِ الدِّينُ الْخَالِصُ ۚ وَالَّذِينَ اتَّخَذُوا مِن دُونِهِ أَوْلِيَاءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللَّهِ زُلْفَىٰ إِنَّ اللَّهَ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ فِي مَا هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي مَنْ هُوَ كَاذِبٌ كَفَّارٌ [٣٩:٣]

<<ንቁ! ፍጹም ጥሩ የኾነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው፡፡ እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች የያዙት «ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም» (ይላሉ)፡፡ አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል፡፡ አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም፡፡ »

የአሐዳዊነት  ቃል  (ላኢላሀ ኢለላሀ) ፍቺው ከአላህ ውጭ በሀቅ ሚገዙት አምላክ የለም፡፡ እስልምናን ለመቀበል የመጀመሪያ ቁልፍ ንግግር ነች፡፡በዚህ ምክን ያት አላህ ፍጥረታትን ገነት እና እሳትን ፈጠረ ፡፡ የሁሉም መልክተኞች ከአባታችን አደም(ዐ.ሰ.ወ) እስከ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የተላኩት በዚሁች ቃል ላይ ነው ፡፡

وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِي إِلَيْهِ أَنَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنَا فَاعْبُدُونِ [٢١:٢٥]

«ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም፡፡»

-የአላህ አንድነት በአምልኮ ውስጥ ከአላህ ውጭ ያለ ማንኛውም አካል ከአምልኮ ማራቅ አምልኮን ለአላህ ማጽደቅ ነው፡፡ እሱላይ አንድንም ነገር አለማጋራት
- የአላህ አንድነት በጌትነት ውስጥ የሁሉም ነገር  የፍጥረታት ሁሉ ፈጠራ የሚያበላ የሚያጠጣ ህያው ሚያረገው ሚገለው በማያጠራጥረው የትናሳኤ ቀን የሚቀሰቅስ  ከአላህ ውጭ የለም፡፡ ፍጥረታትን እነዳሻው ሚያረግ፡፡ ወደ አምልኮ ሚመራ የለም ስራን ከፍ ሚያረግ መከልከልም መፍቀድም የእሱ ስራ ብ ነው ፡፡

هُوَ الْحَيُّ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَادْعُوهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ ۗ الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ [٤٠:٦٥]

«እርሱ ብቻ (ሁል ጊዜ) ሕያው ነው፤ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ ሃይማኖትንም ለእርሱ ያጠራችሁ ስትኾኑ «ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለአላህ ይኹን» የምትሉ ኾናችሁ ተገዙት፡፡»
-የአላህ አንድነት በስሞቹም በባህሪያቶቹ የእሱ ብቻ መሆኑን ለይቶ ማውጣት ሙሉ የሆኑ ባህሪያቱ  ይህች ባህሪ ከጉድለት ከመመሳሰል ነውር የጠራ ነው፡፡

فَاطِرُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَاجًا وَمِنَ الْأَنْعَامِ أَزْوَاجًا ۖ

يَذْرَؤُكُمْ فِيهِ ۚ لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ ۖ وَهُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ [٤٢:١١]

*«ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ነው፡፡ ከነፍሶቻችሁ ሴቶችን ከቤት እንስሳዎችም ዓይነቶችን (ወንዶችና ሴቶችን) ለእናንተ አደረገላችሁ፡፡ በእርሱ ያበዛችኋል፡፡ የሚመስለው ምንም ነገር የለም፡፡ እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡»*

## 3-አምልኮ

አላህ የሰው ልጆችን አላከም እንዲገዙት እንጂ ፡፡

وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ [٥١:٥٦]

*«ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡»*

*አምልኮ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ፍላጎቱ ነው፡፡ ልክ በህይወት ለመቆየት አካላቶቻችን ምግብና ውሀ እንደሚያስፈልጋቸው ነፍሳችን ለስክነት ለእርጋታ አምልኮ መሻት ያለምንም ቅሮት በሰው ልጆች ባአጠቃላይ በግልጽ ይታያል፡፡ የፍላጎታቸውን እርጋታና ስክነት ለማግኘት ወደ አምላካቸው ይጠጋሉ፡፡ ሰዎች ከአባታችን አደም እስከ ኑህ (ዐ.ሰ.ወ) ባለ ዘመን ውስጥ አንድ አላህን ብቻ እየተገዙ ነበር፡፡ነገር ግን የኃላ ኃላ ጠኦት ተፈጠረ ሰዎችም ጣኦት መገዛት ጀመሩ በዚህ ሰአት ድንጋይ ዛፍ እንስሳ የተለያዩ ጣኦቶች በግልጽ መገዛት ማጋራት ተጀመረ፡፡አላህ የለም እስከማለት ደረሱ፡፡ አላህ ከዚህ ይጠብቀን ፡፡ወደ ኢስላም እና አሐዳዊነት እንዲ መልሷቸው መልክተኞች ተላኩ*

## 4-*ምክንያታዊነት*

ኢስላም ለአዕምሮ ትልቅ ክብር እና ቦታ ይሰጣል የቁርአን አብዛኛው አንቀጾች የሚያዙት የሚሰብኩት በማተዋል ማስተን ተን እንዲሰራ ነው፡፡

*አያስተነትኑምን?* أَفَلَا يَتَدَبَّرُون *«አያውቁምን?* أَفَلَا يَعْقِلُونَ

إِنَّ فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ لَآيَاتٍ لِّلْمُؤْمِنِينَ [٤٥:٣]

በሰማያትና በምድር ውስጥ ለምእምናን ሁሉ (ለችሎታው) እርገጠኛ ምልክቶች አልሉ፡፡

وَفِي خَلْقِكُمْ وَمَا يَبُثُّ مِن دَابَّةٍ آيَاتٌ لِّقَوْمٍ يُوقِنُونَ [٤٥:٤]

«እናንተንም በመፍጠር ከተንቀሳቃሽም (በምድር ላይ) የሚበትነውን ሁሉ (በመፍጠሩ) ለሚያረጋግጡ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ፡፡»

وَاخْتِلَافِ اللَّيْلِ وَالنَّهَارِ وَمَا أَنزَلَ اللَّهُ مِنَ السَّمَاءِ مِن رِّزْقٍ فَأَحْيَا بِهِ الْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَا وَتَصْرِيفِ الرِّيَاحِ آيَاتٌ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ [٤٥:٥]

«ጭንቅላታችን ሊያስብ ሊያስተነትን ሊያውቅ ሚችለው የተወሰነለት ን ነው ፡፡ ከኛ ፍላጎት ስሜት የስሜት አካላቶቻችን ባለፈ ያሉ ነገሮች ለጨንቅላታችን ሩቅ ነው፡፡ ማውቅ ሚችለው ስሜትና ፍላጎቱን ብቻ ነው ስለሩቅ አለም ጭንቀላታችን ለማወቅ ምንም ምክነያት የለውም፡፡ ይህን የሩቅ አለም በራሳችን ጥረት እና አዕምሮዐዊ ብቃት ለማወቅ አቅሙ አይደለም፡፡ አላህ ለሰዎች እንዲያብራሩ ከላካቸው አንዳንድ ነብያት በስተቀር ማንም ሊያውቀው አይችልም፡፡»

عَالِمُ الْغَيْبِ فَلَا يُظْهِرُ عَلَىٰ غَيْبِهِ أَحَدًا [٧٢:٢٦]

«(እርሱ) ሩቁን ምስጢር ዐዋቂ ነው፡፡ በምስጢሩም ላይ አንድንም አያሳውቅም፡፡»

የኢስላም አስተምሮት የሰውልጅ ጭነቅላት ሊቀበለው የሚችለው ፍትሐዊና እውነተኛ ጠቃሚ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ክልከላውም ሆነ ትእዛዛቱ ፍትሐዊ ቢሆን እንጂ አላዘዘም አልከለከለም፡፡ ምንም ነገርም አላዘዘም ጠቃሚ ቢሆን እንጂ አንድም ነገር አልተከለከለም ግልጽ አጥፊ ከሆነ ነገር በስተቀር የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ቁርዐን እና የነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) መንገድ ያስተነተነ እውነት አይጋረድበትም፡፡

## 5= __መለኮታዊ__

የኢስላም መለኮታዊ አስተምሮት ከአምልኮ ስነ-ምግባር እና ሙብትና ግዴታ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ይህ ስርዐት ቋሚ እና ተመሳሳይ የሌለው ሊተካ የማይችል ነው፡፡

« ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው፡፡» تَنزِيلٌ مِّن رَّبِّ الْعَالَمِينَ [٥٦:٨٠]

ጥፋት እና የበታች ነት የሰው ልጆች ባህሪ አይደም፡፡ በዙሪያቸው ባሉ ባህል ቅርስ አከባቢ ሁናቴ ተጽእኖ ይፈጥርባቸዋል፡፡

أَفَحُكْمَ الْجَاهِلِيَّةِ يَبْغُونَ ۚ وَمَنْ أَحْسَنُ مِنَ اللَّهِ حُكْمًا لِّقَوْمٍ يُوقِنُونَ [٥:٥٠]

«የማይምንነትን ፍርድ ይፈልጋሉን= ለሚያረጋግጡም ሰዎች ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው=>>

ኢስላም ከመበረዝ ከቅያሪ ከጭማሪ እነዲሁም ከጉድለት የጠራ ብቸኛ ሐይማኖት ነው፡፡ የኢስላም የሕግ ድንጋጌወች መነሻው ከታች የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

1 ፦ የተከበረው ቁዲስ ቁርዐን = በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከወረደበት ሰአት ጀምምሮ እስካለንበት ዘመን ወደፊትም ምንም ነገር ሳይገጥመው እንደወረደ ይቆያል፡፡ ብረዛና ቅነሳ ጭማሪ ሳይገጥመው ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቷል ይቆያል፡፡ በርግጥ ሙስሊሞች የአላህን (ሱ.ወ) ቃል የሆነውን ቁርአን ከአላህ (ሱ.ወ)ምንዳን በመሻት በመማር በማስተማሩ ላይ ይሽቀዳደሙ ነበር፡፡ የነብዩ ሙህመድ (ሰ.ዐ.ወ) እነዳወሩት፡፡

ዑስማን ኢብን ዐፉፍን (ረ.ዐ)እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)እንዲህ ብለዋል «ከእናንተ ውስጥ በላጩ ቁርዐንን ተምሮ ያስተማረ ነው፡፡»

ስለዚህ ሰዎች በልቦናቸው በመሽምደድ እና በማንበብ አላህን ይገዛሉ፡፡ የነብዩ ሙህመድ (ሰ.ዐ.ወ) እነዳወሩት «ከቁርዕን አንድ ቃል ያነበበ ለሱ አስር የበጎስራ ምንዳ አለው አ.ላ.ም አንድ ፊደል ነው አልላችሁም ነገር ግን አሊፍ አንድ ፊደል ነው ላም አንድ ፊደል ነው ሚም አነድ ፊደል ነው፡፡

2፦ ሁለተኛው የሸሪዐ ምንጭ የተከበረው የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር ቁርዐን የተብራራበት እና ቁርዐን የሚያብራሩ ሰዎች ውሳኔ በመስጠት ቁርአንን ያብራረሩበት ነው፡፡እንዲሁም ቁርዐንን ከጭማሪ ተንኮል ሴራ በዚህ ተጠብቋል፡፡ ከአላህ ጥበቃ በመቀጠል በተወሰኑ ሰዎች ጥረት ነፍሳቸውን ነጻ አርገው ጊዜያቸውን ሕይወታቸውን በመሰዋት የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ በጠቅላላ ለመማር አመጣጡን አጻጻፉን ጠንካራና እና ደካማ የሐዲሱን ሁኔታ እና ደረጃ ማስተካከል ጉድለቱን ማጥራት አቆይተውታል፡፡

## 6 አለም አቀፋዊ ሐይማኖት

ኢስላም አለም አቀፋዊ እምነት ነው፡፡ በሰው ልጅ መገኛ በጠቅላላ ያለምንም ከልካይ ነጩም ጥቁሩም አረቡም አለረብ ያልሆነው በሁሉም ቦታ ዘመን ቀለም ቦታ ጊዜ በመዳረሱ ምንም መሰረት ያላረገ እምነት ነው፡፡ ግልጽ እውነትነቱ የተተረጋገጠ ሁሉንም ያጠቃለለ እንዲሁም በአላህ ጌትነት በኢስላም እምነት በነብዩ መሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) በማንኛውም ቦታና ጊዜ ያመነ ሁሉ ኢስላም ባንዲራ ስር ተጠቃሎ ይገባል፡፡ በርግጥ ለተወሰኑ ህዝቦች ለተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ሙሳን(ዐ.ሰ.ወ) ለእስራኤል ልጆች ህግጋት ይዘው እነደተላኩት አላህ (ሱ.ወ) በቁርዐን እንደተናገረው

وَآتَيْنَا مُوسَى الْكِتَابَ وَجَعَلْنَاهُ هُدًى لِّبَنِي إِسْرَائِيلَ أَلَّا تَتَّخِذُوا مِن دُونِي وَكِيلًا [١٧:٢]

«ሙሳንም መጽሐፉን ሰጠነው፡፡ ለእስራኤልም ልጆች መሪ አደረግነው፡፡ ከእኔ ሌላ መጠጊያን አትያዙ፤ (አልናቸውም)፡፡»

አእስራኤል ልጆች በነበዩላህ ሙሳ(ዐ.ወ) ይዘው የመጡት መልእክት ጊዜ በረዘመ ቁጥር የተብራራላቸውን የአላህ ቃልኪዳን ንደው ከትክክለኛው ጎዳና ሲወጡ አላህ በደጋሚ ኢሳ (ዐ.ሰ.ወ) ወደትክክለኛው ጎዳና እንዲመልሷቸው ተለኩ፡፡ አላህ በቁርዐን እነደገለጸው

وَقَفَّيْنَا عَلَىٰ آثَارِهِم بِعِيسَى ابْنِ مَرْيَمَ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ التَّوْرَاةِ ۖ وَآتَيْنَاهُ الْإِنجِيلَ فِيهِ هُدًى وَنُورٌ وَمُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ التَّوْرَاةِ وَهُدًى وَمَوْعِظَةً لِّلْمُتَّقِينَ

[٥:٤٦]

‹‹በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፡፡ ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው፡፡»

በጊዜያት ሂደት በኃላ ለሰው ልጅ ለጂን በአጠቃላይ አላህ(ሱ.ወ) ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላከላቸው፡ ፡ በእሳቸው አማካኝነት መልእክቱ ተደመደመ  አላህ(ሱ.ወ) በቁርዐኑ እነደገለጸው

تَبَارَكَ الَّذِي نَزَّلَ الْفُرْقَانَ عَلَىٰ عَبْدِهِ لِيَكُونَ لِلْعَالَمِينَ نَذِيرًا [٢٥:١]

«ያ ፉርቃንን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስፈራሪ ይኾን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብርና ጥራት ተገባው፡ ፡አለም አቀፋዊ በመሆኑ የሰው ልጆች ይህን ዲን ለመቀበል አይጠሉም ነገር ግን መልክቱ የደረሰውን የተብራራለትን ሰው የመምረጥ የመቀበል ያለመቀበል  ነጻ ምርጫ አለውእጣው ጥሜት እንዳይሆን አብራራለት በቁርአን እንተገለጸው»

وَقُلِ الْحَقُّ مِن رَّبِّكُمْ ۖ فَمَن شَاءَ فَلْيُؤْمِن وَمَن شَاءَ فَلْيَكْفُرْ ۚ إِنَّا أَعْتَدْنَا لِلظَّالِمِينَ نَارًا أَحَاطَ بِهِمْ سُرَادِقُهَا ۚ وَإِن يَسْتَغِيثُوا يُغَاثُوا بِمَاءٍ كَالْمُهْلِ يَشْوِي الْوُجُوهَ ۚ بِئْسَ الشَّرَابُ وَسَاءَتْ مُرْتَفَقًا [١٨:٢٩]

«እውነቱም ከጌታችሁ ነው፡፡ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው፡፡ እኛ ለበደለኞች አጥሯ በእነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል፡፡ (ከጥም) እርዳታንም ቢፈልጉ እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ ይረዳሉ፡፡ መጠጡ ከፋ! መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች!>>

# 7 ሚዛናዊነት

ሚዛናዊቱ ለኢስላም መስፋፋትን አግዞታል፡፡ ኢስላም ሚዛናዊ እና ካለንበት አለም ከመጪዊም አለም መሃል የሆነ ለመረዳትም ሆነ ለማወቅ የገራ መሆኑ ልዩ ያረገዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛ እንዳስተላለፉት ከዲን ሁሉ ተወዳጁዋ ቀጥ ያለችው የአላህ ዲን ናት፡፡

በእርግጥ ኢስላም በንግግርም ሆነ በተግባር የሰው ልጅን ካቅሙ በላይ አላሸከመውም፡፡ ከተፈጥሮ ጋር የማይጋጭ ሰላማዊ ጉርብትና ያለው ለአምልኮ ምቹ ከሁናቴዎችጋ እና ከውሳኔዎች ጋር የሚስማማ ሀይማኖት እንዴት የተፈጥሮ ሐይማኖት ሊሆን አይችልም፡፡

وَمَا جَعَلَ عَلَيْكُمْ فِي الدِّينمِنْ حَرَجٍ

«በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፡፡»

ስለዚህ የህግጋቱ መቅለል የምልኮው መግራት እና ቀለል ማለት የሰዎችን አቅማቸውን እና ችሎታቸውን እና የሰዎችን ችግር በማገናዘብ ነው፡፡ሁሉም ኢስላማዊ ትዕዛዛት ከሰው ልጆች አቅምና ችሎታ ጋር የገጠመ ሆኖ ነው የወረደው፡፡ ከአቅሙ በላይ አላስገደደውም፡፡ አምልኮአዊም ሆነ አለማዊ ጉዳዮች ላይ ለችግሩ መፍትሄ የሚሆኑ ሀይማኖታዊ ድንጋጌዎች አሉት፡፡

فَمَنِ اضْطُرَّ غَيْرَ بَاغٍ وَلَا عَادٍ فَلَا إِثْمَ عَلَيْهِ ۚ

«ሸፍታና ወሰን አላፊ ሳይኾን (ለመብላት) የተገደደ ሰውም በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም»

አላህ(ሱ.ወ) የሰውን ልጅ ደካማ አርጎ ፈጠረው፡፡ የሰውልጅ ጉድለት የሚያገኘው አቅሙ የተገደበ ፍጥረት ነው፡፡ ስለሆነም ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር ሊሰማሚ የሆነ ሊጠበቅበት እና ሚጠቅመው የሆነን ህግ እና ደንብ አወረደለት፡፡

يُرِيدُ اللَّهُ أَن يُخَفِّفَ عَنكُمْ ۚ وَخُلِقَ الْإِنسَانُ ضَعِيفًا [٤:٢٨]

«አላህ ከእናንተ ሊያቃልልላችሁ ይሻል፡፡ ሰውም ደካማ ኾኖ ተፈጠረ፡፡»

የኢስላም ትእዛዛት የተገነባው በአምልኮ መንገድ ላይ ነው፡፡

لَا يُكَلِّفُ اللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا لَهَا مَا كَسَبَتْ وَعَلَيْهَا مَا اكْتَسَبَتْ

«አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፡፡ ለርስዋ የሠራችው አላት፡፡»

የአላህ መልዕክተኛ እንዳስተላለፉት (ሰ.ዐ.ወ) «ከከለከልኳችሁ ነገር ራቁ የታዘዛችሁትን በምትችሉት አቅም ስሩ በፊት እንደነበሩት ሕዝቦች ጥጣቄ በማብዛታቸው ከነብያቸውጋ ተለያዩ»

አንድ ማወቅ ያለብን ነገር የኢስላም ሀይማኖት መልካም እና ቀላልነቱ ባለፈ

ልናውቀው ሚገባ ነገር ዲንን ማግራራት ማለት የሀይማኖት ህግጋትን መጣስ ክልክሉን መፍቀድ የተፈቀደውን መከልከል አይደለም ይህ ማለት ህግጋቱን በማዛባት ትእዛዙን በማስተባበል የእስልምናን ጽንሰ ሀሳብ ስነ-ምግባሩን መጣስ ነው፡፡ ነገርግን ማግራራት ለሰወች በማይቸግር እና በማይከብድ ሁኔታ እንዲሰሩት በማረግ ከወንጀል ሰዎችን ማራቅ ነው፡፡

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ባሌቤት ከድጃ (ረ.ዐ) እንዳወሩት ከሁለት ነገሮች ምህል የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)ምራጫቸው ቀለል ያለውን ነበር፡፡ ለሰው ልጅ ሚነዳና ወንጀል ከሆነ ይርቁታል፡፡

## 8 ሙሉዕ እና መደምደሚያ

ኢስላም ሙሉዕ የሆነ ሐይማኖት ነው፡፡ አላህ(ሱ.ወ) ሙሉዕ አርጎ ያለፉ ሀይማኖታዊ ህግጋት መደምደሚያ በጸጋው የሞላው ለባሪያዎቹ የመረጠው ሐይማኖት ነው፡፡

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا ۚ

«ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡»

በዚህ ሙሉ ባረገው ሀይማኖት ያለፉትን ሀይማኖታዊ ድንጋጌዎችን ሰርዟል፡፡ ከሱ ውጭ ለሚገዙ ሰዎች አምልኮዋቸውን አይቀበልም ፡፡ከዚህ ቀደም የነበሩ ሐይማኖታዊ ህግጋት መንፈሳዊ ህግጋት ሲሆኑ ግኙኝነታቸው ከነፍስጋ ነፍስንም መቆጣጠር ብቻ ነበር፡፡ ሙሉዕ በሆነ ሁናቴ አለማዊ የኑሮ ሁኔታ በማስተካከል በመቆጣጠር ስርአት በማስያዙ በኩል ከኢስላም በተቃራኒ ነው ፡፡ኢስላም አለማዊም የመጪውን አለም አጠቃሎ የሕይወት አቅጣጫ ለማስተካከል ሙሉ ለማረግ የመጣ ዲን ነው፡፡ በርግጥ ነቢዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ይህን እውነታ አብራርተውልናል፡፡ ይህ ዲን አላህ(ሱ.ወ)ዘንድ አንድ ነው ፡፡ አላህ (ሱ.ወ)ነብየትን አንዱን በአንዱ ላይ እንዲሞላ ልኳል በኑህ (ዐ.ሰ.ወ) በመጀመር በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ድምዳሜነት ተደመደመ ህግጋቱም ተሟሉ፡፡

በዚህ ደምዳሜና ሙሉነት መሰረት አላህ (ሱ.ወ) የኢስላምን ሐይማኖት ለመጠበቅ ቃል ገብቷል ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ከዚህ ቀደም ከነበሩት ሐይማኖቶች በተለየ ሁኔታ ቃል ላልገባላቸው እና ለተወሰኑ ህዝቦች እና ዘመናት ከወረደው ሐይማኖት በተለየ ሁኔታ ምድርን እና በውስጧ ያሉትን አውርሷል፡፡

إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ [١٥:٩]

«እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡>>

## 9 ግልጽ እና አንጸባራቂ

ኢስላም ግልጽ ብሩህ የሆነ ሐይማኖት ነው፡፡ የልተሸፋፈነ የልተጋረደ ለኢስላም የመጀመሪያ ህግጋት ምንጭ ቁርዐን ግልጽ የሆነ ለሰዎች ቀጥተኛውን ጎዳና ገላጭ ግልጽ ማስረጃ እና ግልጽ የመሆኑ ማብራሪያ ነው፡፡

قَدْ جَاءَكُم مِّنَ اللَّهِ نُورٌ وَكِتَابٌ مُّبِينٌ [٥:١٥]

«ከአላህ ዘንድ ብርሃንና ገላጭ መጽሐፍ በእርግጥ መጣላችሁ፡፡»

በደፈናው አስተሳሰብን መቀበል ተቀባይነት የለውም፡፡ የሰው ልጅ ያስቸገረውን ጭንቅላቱ ውስጥ ለሚፈጠሩ ጥያቄዎች የመጠየቅ ሙሉ መብት አለው፡፡ ያለ እውቀት እንድንጋተር ጥሪ አልተደረገልንም፡፡ እንደውም በያንዳንዱ ሐይማኖታዊ ጉዳይ እንድንወያይ መብት አስቀምጦልናል፡፡ እውቀት የእውቀት ባለቤቶቸ ጋር ይገኛል፡፡ እነዚህ ሰዎች ነፍሳቸውን ነጻ አርገው እነደየ ዘረፉ እውቀት ሲያጠኑ የነበሩ ህግጋት ጉዳዮች በህግ ጉዳይ ብቁ የሆኑ አካላት ዘንድ ህክምና ከሀኪሞች ዘንድ ምህንድስና ከመሀንዲስ እጅ  እስላማዊም እውቀት ሚገኘው ነፍሱን በዚህ ጥናት ላይ ካረገ ሰው ነው፡፡

وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ إِلَّا رِجَالًا نُّوحِي إِلَيْهِمْ ۚ فَاسْأَلُوا أَهْلَ الذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ

[١٦:٤٣]

«ከአንተም በፊት ወደእነሱ ወሕይን (ራእይን) የምናወርድላቸውን ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም፡፡ የማታውቁም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ፡፡>>

በኢስላም ውስጥ ያልገባንን  ሳንጠይቅ ያለምክንያት ምናምንበት ጉዳይ የለም፡፡አለህ (ሱ.ወ) ለሰዎች ያለብራራው የሩቅ አለም ማወቃችን ጥቅም የሌለው ነገር ሲቀር፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በሩቅ አለም ያመኑ ሰዎችን ጥቅም ያብራራል ላላመኑ አካላትም ፈተና ነው፡፡

الم [٢:١] ذَٰلِكَ الْكِتَابُ لَا رَيْبَ فِيهِ هُدًى لِّلْمُتَّقِينَ [٢:٢]

«ይህ መጽሐፍ (ከአላህ ለመኾኑ) ጥርጥር የለበትም፤ ለፈራህያን መሪ ነው፡፡»

الَّذِينَ يُؤْمِنُونَ بِالْغَيْبِ وَيُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنفِقُونَ [٢:٣]

«ለነዚያ በሩቁ ነገር የሚያምኑ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀው የሚሰግዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚቸሩ ለኾኑት፤
»

وَالَّذِينَ يُؤْمِنُونَ بِمَا أُنزِلَ إِلَيْكَ وَمَا أُنزِلَ مِن قَبْلِكَ وَبِالْآخِرَةِ هُمْ يُوقِنُونَ [٢:٤]

«ለእነዚያም ወደ አንተ በተወረደውና ከአንተ በፊትም በተወረደው የሚያምኑ በመጨረሻይቱም (ዓለም) እነርሱ የሚያረጋግጡ ለኾኑት (መሪ ነው)፡፡»

أُولَٰئِكَ عَلَىٰ هُدًى مِّن رَّبِّهِمْ ۖ وَأُولَٰئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ [٢:٥]

«እነዚያ ከጌታቸው በመመራት ላይ ናቸው፤ እነዚያም እነሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው፡፡»

## 10 : መልካምነት

ኢስላም በተፈጥሮው መልካም በዙሪያው ካካበቡት ፍጥረታታት አሉታዊ ያልሁነ በጎነቱ ፍጡራንን ያጠቃለለ እምነት ነው፡፡ ይህ ኢስላም ብሩህ የሆነ መልካምን ነገር እንድናስፋፋ ለራሳችን ለሌላም አካላት እንድንወድላቸው ያዘዘ እምነት ነው፡፡ ለራሳችን ብቻ መልካም መሆን በቂ አይደለም እንዲያውም ለሌሎች መልካም እና በማህበረሰቡ ላይ ተጽዕኖ ማሳዳሪ መሆን አለበት፡፡ መልካምን ስራ እውቀትን በማስፋፋት የጠመመን እያቃና ከመጥፎ እየከለከለ አላህን ብቻ እንዲገዙ ጥሪ እያረገ ሚኖር ነው፡፡

وَلْتَكُن مِّنكُمْ أُمَّةٌ يَدْعُونَ إِلَى الْخَيْرِ وَيَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنكَرِ ۚ وَأُولَٰئِكَ
هُمُ الْمُفْلِحُونَ [٣:١٠٤]

«ከናንተም ወደ በጎ ነገር የሚጠሩ በመልካም ሥራም የሚያዙ ከክፉ ነገርም የሚከለክሉ ሕዝቦች ይኑሩ፡፡ እነዚያም እነሱ የሚድኑ ናቸው፡፡»

ኢስላም ህግጋት ለሰው ልጆች መልካምነትን እና በጎነትን እንዲወዱ በአምልኮ ሙሉ ተደረገ፡፡(

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት«ለራስህ የወደድከውን ለሌሎች ውደድ ሙስሊም ትሆናለህ»)

ለመልካም ነገር ማነሳሳት ማነቃቃት በጎ ነገርን በማስፋፋት ኢስላም ከፍያለና የላቀቦታ ሰጥቶታል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) «ወደ መልካም ነገር ጥሪ ያረገ ተከተለው ሰው በሚያገኘው የበጎስራ ክፍያ ምንም ሳይቀነስ ለሱም የበጎ ስራ ክፍያ አለው፡፡ወደ ጥፋት ያመላከተ ለሱ ከተከተሉት ምንም ሳይጎል ከወንጀሉ አለው፡፡»

## 11 <u>ጽናት እና ለውጥ</u>

ኢስላም ለውጥን ከመፈለግ ጋር ቁርኝት ያለው ለውጥን ያካተተ ሐይማኖት ነው፡፡ይህ ነገሩ ኢስላምን በየትኛውም ዘመንና ቦታ ልዩ ተመራጭ እና መልካም ያረገዋል፡፡ የኢስላም መለኮታዊ ህግጋት ባጠቃላይ በየትኛውም ዘመን እና ቦታ ሊቀየር ሊለወጥ የማይችል ቃሚ የሆነ የሰላትን የቁጥር ብዛት ጊዘያቸውን የዘካን የግዴታ ገደብ የጾም ወቅት የሐጅ ሁኔታ የጊዜ የቦታ ገደብ ..........ወዘተ የመሳሰሉ

እኚህን ነገሮች በቅድሚያ ቁርዐን ውስጥ የሰፈሩ ክስተቶችን መመልከት ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መናገራቸው እውነትነቱ ወደተርጋገጠ ንግግራቸው መዘንበል ከሁለቱ በአንዳቸው ከተገኘ አጥብቆ መያዝ ያ በመቀጠል ኡለሞች የእውቀት ባለቤቶች እይታ መመልከት ይህ ሚሆነው በየትኛውም ዘመንና ቦታ ለሰዎች ህዝባዊ ጥቅምና የህብረተሰቡ ሁኔታ አግባብ ባለው አስፈላጊነቱ በተረጋገጠበት ቁርዐን እና ሐዲሶችን በመገምገም እንዲሁም ከቁርዐንና ሀዲስ የሆኑ ጠቅላላ ህግጋትን በማየት ነው፡፡ሰዎችን ያለተቃውሞ ወደ ጠቃሚ ነገር ለማድረስ ነው፡፡ ኢስላም የሁሉም ዘመናት ሰዎች በቁርኝት ተግባብቶ እንዲኗዝ ማስቻል ነው፡፡በርግጥ ይህ መስፈርት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሙዐዝ ኢብን ጀበልን የመን ለመላክ በወሰኑ ግዜ የተጠቀሙት መስፈርት ነው፡፡

### 12 <u>ሙሉዕነት</u>

እስልምና የሰውን ልጅ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎት በሚዛናዊ ሁኔታ ተቀብሎ ያስተናግዳለ፡፡

وَابْتَغِ فِيمَا آتَاكَ اللَّهُ الدَّارَ الْآخِرَةَ ۖ وَلَا تَنسَ نَصِيبَكَ مِنَ الدُّنْيَا ۖ وَأَحْسِن كَمَا أَحْسَنَ اللَّهُ إِلَيْكَ ۖ وَلَا تَبْغِ الْفَسَادَ فِي الْأَرْضِ ۖ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُفْسِدِينَ [٢٨:٧٧]

«አላህም በሰጠህ ሀብት የመጨረሻይቱን አገር ፈልግ፡፡ ከቅርቢቱም ዓለም ፋንታህን አትርሳ፡፡ አላህም ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ (ለሰዎች) መልካምን አድርግ፡፡ በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፡፡ አላህ አጥፊዎችን አይወድምና» (አሉት)፡፡››

የሰው ልጅ መንፈስ በኢስላም እይታ አላህ (ሱ.ወ) የፈጠረው በምድር ላይ የተሾመው ሙሉ አርጎ የሰጠውን አካል በመጠቀም አላህ ባዘዘው ባወረደለት ህግና ደንብ መሰረት አላህን ኢነዲገዛ ነው፡፡ ምድርንም የማበልጸግ ሙብትን ተሰጥቶታል፡፡

وَهُوَ الَّذِي جَعَلَكُمْ خَلَائِفَ الْأَرْضِ وَرَفَعَ بَعْضَكُمْ فَوْقَ بَعْضٍ دَرَجَاتٍ لِّيَبْلُوَكُمْ فِي مَا آتَاكُمْ ۗ إِنَّ رَبَّكَ سَرِيعُ الْعِقَابِ وَإِنَّهُ لَغَفُورٌ رَّحِيمٌ [٦:١٦٥]

«እርሱም ያ በምድር ምትኮች ያደረጋችሁ በሰጣችሁም ጸጋ ሊፈትናችሁ ከፊላችሁን ከከፊሉ በላይ በደረጃዎች ከፍ ያደረገ ነው፡፡ ጌታህ ቅጣቱ ፈጣን ነው፡፡ እርሱም እጅግ መሐሪ ሩኅሩኅ ነው፡፡»

በኢስላም አላህ ለባርያው የፈቀደለትን የዱንያ ጥፍጥና ጣዕም ጥሩውን ጣቃሚውን ነገር በመራቅ መመንኮስ የተከለከለ ነው፡፡

قُلْ مَنْ حَرَّمَ زِينَةَ اللَّهِ الَّتِي أَخْرَجَ لِعِبَادِهِ وَالطَّيِّبَاتِ مِنَ الرِّزْقِ ۚ قُلْ هِيَ لِلَّذِينَ آمَنُوا فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا خَالِصَةً يَوْمَ الْقِيَامَةِ ۗ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ الْآيَاتِ لِقَوْمٍ يَعْلَمُونَ [٧:٣٢]

«የአላህን ጌጥ ያችን ለባሮቹ የፈጠራትን ከሲሳይም ጥሩዎቹን እርም ያደረገ ማን ነው?» በላቸው፡፡ «እርሷ በትንሣኤ ቀን ለእነዚያ ላመኑት ብቻ ስትኾን በቅርቢቱ ሕይወት ተገቢያቸው ናት» በላቸው፡፡ እንደዚሁ ለሚያውቁ ሕዝቦች አንቀጾችን እናብራራለን፡፡»

እንደዚውም በዱንያዊ ብልጭልጭ ስሜት ጥፍጥና በመማረክ ፊቱን ወደ ዱንያ ያረገ ሐይማኖት ሳይሆን በአለማዊም በመንፈሳዊ ስሜታችን ፍትሐዊ በሆነ ሚዛናዊነት በመሆን ሰዎችን በማዘዝ የሰበከ እምነት ነው፡፡ ነፍስ በስጋዊ ስሜቶች ውስጥ ስትዋጥ ወደፈጣሪዋ መለስ እንድትል በማስታወስን ግዴታ የሆኑባትን ነገር እዲፈጽም ታዟዋል፡፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِذَا نُودِيَ لِلصَّلَاةِ مِن يَوْمِ الْجُمُعَةِ فَاسْعَوْا إِلَىٰ ذِكْرِ اللَّهِ وَذَرُوا الْبَيْعَ ۚ ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ [٦٢:٩]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በዐርብ ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ኺዱ፡፡ መሸጥንም ተዉ፡፡ ይህ የምታውቁ ብትኾኑ ለእናንተ በጣም የተሻለ ነው፡፡»

አምልኮ ውስጥም ሆነን ሳለ ሳጋዊ ስሜታችን ማማላት እንዳለብን ታዘናል፡፡

فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِن فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيرًا لَّعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ [٦٢:١٠]

«ሶለቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡»

ኢስላም እኝህን የሁለት አለም ባሕርያትን አማልቶ የያዘን አካል ያሞግሳል፡፡

رِجَالٌ لَّا تُلْهِيهِمْ تِجَارَةٌ وَلَا بَيْعٌ عَن ذِكْرِ اللَّهِ وَإِقَامِ الصَّلَاةِ وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ ۙ يَخَافُونَ يَوْمًا تَتَقَلَّبُ فِيهِ الْقُلُوبُ وَالْأَبْصَارُ [٢٤:٣٧]

«አላህን ከማውሳትና ሶላትን ከመስገድ ዘካንም ከመስጠት ንግድም ሽያጭም የማያታልላቸው ልቦችና ዓይኖች በእርሱ የሚገላበጡበትን ቀን የሚፈሩ የኾኑ ሰዎች (ያጠሩታል)፡፡>>

ኢስልምና በአምልኮ ህግጋት መሰረት የሰውን ልጅ አካላዊ መንፈሳዊ መብቶች ይጠብቃል፡፡ እንደተራ ነገር ችላ በማለት አልተወውም ፡፡ በዚህ ምክንያት የሰውልጅ በነፍሱ ጥበቃ ይጠየቅበታል፡፡በየስራው ለነፍሱ ቅድሚያ በመስጠት ይተሳሰባታል፡፡

فَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ خَيْرًا يَرَهُ [٩٩:٧]

«የብናኝ ክብደት ያክልም መልካምን የሠራ ሰው ያገኘዋል፡፡»

وَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ شَرًّا يَرَهُ [٩٩:٨]

«የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሠራ ሰው ያገኘዋል፡፡»

እንደዚሁም አንድ ሙስሊም የሆነ ግለሰብ ለአካሉ አላህ በሰጠው በያንዳንዱ ጸጋዎች ይጠይቀዋል፡፡ እንደ ምግብ መጠጥ ልብስ እነዚህን መሰል ጸጋዎች ያለማባከን ጉዳት ሳያደርሱበት በመቆጣጠር መጠቀም አለበት፡ ፡

وَكُلُوا وَاشْرَبُوا وَلَا تُسْرِفُوا ۚ إِنَّهُ لَا يُحِبُّ الْمُسْرِفِينَ [٧:٣١]

«ብሉም፤ ጠጡም፤ አታባክኑም፡፡ እርሱ አባካኞችን አይወድምና፡፡»

ኢስላም የክልከላ ግንዛቤ ሊከለክል ሚችለው በኢስም ህግጋት ክልከላ መሰረት አድርጎ ነው፡፡

አነስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ፡ ሰዎች ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች ቤት መጡ ፡፡ ስለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አምልኮ ለመጠየቅ ሲነገራቸው ቀለል አድርገው ተመለከቱት፡፡ «ያለፈውም የሚመጣውም ውነጅላቸው ይቅር የተባለላቸው ነብይ በኢባዳ ከኛጋር ሚወዳደሩ አይደሉም» አሉ፡፡ ከመሐከላቸው አንዱ «እኔ ሁሌም ስሰግድ አድራለሁ»አለ፡፡ ሌላኛው ደግሞ «እኔ ደሞ ዓመቱን ሙሉ በጾም አሳልፋለሁ» ሲል፡፡ የመጨረሻው ደግሞ «እኔ ከሴት እርቃለሁ፡፡ እስከ ወድያኛው አላገባም» በማለት ተናገረ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)ወደ እነርሱ መጡና «እናንተ ናችሁ እንዲህ እንዲህ ያላችሁት ? በአላህ እምላለሁ እኔ ከናንተ ይበልጥ አላህን እፈራለሁ  እጠነቀቃዋለሁም ነገር ግን እጾማለሁ ጾም እፈታለሁ፡፡ እሰግዳለሁ እተኛለሁ ሴትም አገባለሁ፡፡ ከኔ ሱንና ያፈነገጠ እኔን አልተከተለም» አሉ፡፡

### 1-<u>ተከታታይ ዘውታሪ</u>

ኢስላም ከአላህ የተላከ የመጨረሻ የመደምምያ ህግ ነው፡፡ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ያለገደብ ባጠቃላይ ጠቃሚ ነው፡፡ ካለፉት አምላካዊ ህግጋት በተለየ ከመበረዝ ከመቀነስ በመጠበቅ ያግዘዋል፡፡ ይህ የመጀመርያው የኢስላም ህግጋት ምንጭ የሆነው ቁርዐን ከጉድለት የተጠበቀ የሆነ ከሁሉም ሐይማኖታዊ መጽሐፍ በተለየ ሁኔታ ለነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የተሰጠ ዘውታሪ ተአምር ነው፡፡ የሌሎች መልክተኞች መልእክት እውነታ በተላኩበት ዘመን ቦታ የተገደበ ነው፡፡ የቁርዐን ተአምርነት እስከ እለተ ትንሳኤ የጸና ነው፡፡ የነብዩ ሙሐመድ መልእክት እውነታነቱን ማረጋገጫ ነው ፡፡

إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ [١٥:٩]

«እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡»

«ከኡመቴ አንድም ጀምዐ አይወገድም እውነት የተረዱ ቢሆኑ እንጂ አይጎዱዋቸውም አያዋርዱዋቸውም እነሱን የተቃረኑዋቸው እስከ እለተ ትንሳኤ፡፡»

በአሁኑ ሰአት እየተመለከትን ያለነው ሰፊ ቁጥር ያለው የሌላ ሐይማኖት ተከታይ  አካላት ኢስላምን ሲቀላቀሉ ቁሳዊ ንብረት የሌላቸው ደካሞች ሆነው ነው፡፡ ቁሳዊና ሰዋዊ ዱጎማ ሳይደረግላቸው ምንም ሳይጠብቁ እንዲሁም የጠላትን ጦር ኢስላም ላይ የተሰነቀረውን የባላንጣዎቻቸው የስም ማጥፋት ሴራ እያዩ ኢስላም ጥላ ስር እተጠሉ ነው፡፡ እስላምን ከተቀላቀሉ በኃላ ተመልሰው ሚወጡት ጥቂት ቁጥር ነው፡፡

## 13 <u>አጠቃላይ ይዘት</u>

የኢስላም  አጠቃላይ ይዘት የሰው ልጅ ሕይወት  በማስተካከል እና ህግ በማውጣት የተሸለ ምሳሌ ሊሆን ሚችል መልካም ስብዕና ባለቤት የሆነ ማህበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ በህይወት ጎዳና ላይ ያስቀረው በሐይማኖታዊ በአለማዊ በግልሰብ በማህበረሰብ አንዳችም ነገር የለም፡፡

وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ الْكِتَابَ تِبْيَانًا لِّكُلِّ شَيْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ [١٦:٨٩]

«መጽሐፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ፣ መሪም፣ እዝነትም፣ ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው::»

የኢስልምና ይዘት የአንድ ሙስሊም ስርዐት ከጌታው እንዲሁም ከማህበረሰቡ ካአጠቃላይ አለም ጋር ባለው ግኑኝነት ላይ ያተኮረ ነው:: ይህ ማለት በመህበረሰባችን ውስጥ ትኩረት የሌላቸውን መልካም ስነ-ምግባራትን ማካተት የኢስላም ፍላጎት እንደሆነ ያመላክታል::

በዚህም ምክንያት ባጠቃላይ ባህሪ ላይ የተመሰረተ ሐይማኖት ነው:: ከነዚም ምህል

⁜ ሰውን ማክበር ከፍጥረታት ሁሉ መርጦ ያላቀው ነገራትን ያገራለት ፍጡር ነው::

وَلَقَدْ كَرَّمْنَا بَنِي آدَمَ وَحَمَلْنَاهُمْ فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ وَرَزَقْنَاهُم مِّنَ الطَّيِّبَاتِ وَفَضَّلْنَاهُمْ عَلَىٰ كَثِيرٍ مِّمَّنْ خَلَقْنَا تَفْضِيلًا [١٧:٧٠]

«የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው:: በየብስና በባህርም አሳፈርናቸው:: ከመልካሞችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው:: ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው::»

⁜ ትውውቅ ከፍጥረታት ጋር በመልካም ግኑኝነት ከሙስሊሙ ማህበረሰብ በማህበሩ ዙሪያ ባሉ ጥሩ ጉርብትና መልካምን ስራ ወዶ መልካምነትን መጋራትን መፍጠር::

يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا ۚ إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ [٤٩:١٣]

«እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ:: እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ:: አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው:: አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው::»

⁜ **አንድነትን መቀበል** አላህ (ሱ.ወ) በሙስሊሞች መሀል የአንድ ወንድሙን ጉዳይ እንደራሱ እነዲመለከት ግዴታ አርጎታል::

የአላህ መልእክተኛ እዳወሩት: «ሙስሊሞችን ትመለከታለህ የመዋደዳቸው የመተዛዘናቸው የመተሳሰባቸው ነገር ልክ እንደ አንድ ሰውነት ይመስላል አንዱ የሰውነት ክፍል ሲታመም ሌሎቹ የሰውነት ክፍሎችም እንቅልፍ በማጣትና በትኩሳት ስቃዩን ይካፈላሉ::»

፨ በስርአት የተገደበ ነጻነት ይህ ነጻነት ከኢስላም ጋር ሳይጋጭ ሰውነቱን የጠበቀ ነጻነት ነው።

1-የሀሳብ ነጻነት አመለካከትን የመግለጽ

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَقُولُوا قَوْلًا سَدِيدًا [٣٣:٧٠]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ።»

**2-ንብረት የማፍራት ነጻነት በተፈቀደለት ስራ**

لِّلرِّجَالِ نَصِيبٌ مِّمَّا اكْتَسَبُوا ۖ وَلِلنِّسَاءِ نَصِيبٌ مِّمَّا اكْتَسَبْنَ ۚ

«ለወንዶች ከሠሩት ሥራ እድል አላቸው። ለሴቶችም ከሠሩት ሥራ ዕድል አላቸው።»

**3-የመማር የማስተማር ነጻነጽ**

**"قول رسول الله صلى الله عليه وسلم" طلب العلم فريضة على كل مسلم ومسلمة**

የአለህ መልክተኛ እንደተናገሩት «እውቀትን መፈለግ ግዴታ ነው።»

**4-የመጠቀም ነጻነት አላህ የፈቀደለትን መልካም ነገሮች የመጠቀም ነጻነት**

هُوَ الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الْأَرْضَ ذَلُولًا فَامْشُوا فِي مَنَاكِبِهَا وَكُلُوا مِن رِّزْقِهِ ۖ وَإِلَيْهِ النُّشُورُ

[٦٧:١٥]

«እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው። በጋራዎችዋና በመንገዶችዋም ኺዱ።፡ ከሲሳዩም ብሉ። (ኋላ) መመለሻውም ወደእርሱ ብቻ ነው።»

**፨ አጠቃላይ ሠላም**

ሰላም በኢስላም፦ ሌላን አካል ሳናጋራ በፍጹም በሆነ ሁኔታ አላህን መገዛት

وَقَاتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ الَّذِينَ يُقَاتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوا ۚ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ

[٢:١٩٠]

«እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፡፡ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎን አይወድምና፡፡»

**= በነፍስ ላይ ሰላም ፦**

وَمَن يَقْتُلْ مُؤْمِنًا مُّتَعَمِّدًا فَجَزَاؤُهُ جَهَنَّمُ خَالِدًا فِيهَا وَغَضِبَ اللَّهُ عَلَيْهِ وَلَعَنَهُ وَأَعَدَّ لَهُ عَذَابًا عَظِيمًا [٤:٩٣]

«ምእመንንም አስቦ የሚገድል ሰው ቅጣቱ በውስጧ ዘውታሪ ሲኾን ገሀነም ናት፡፡ አላህም በርሱ ላይ ተቆጣ፡፡ ረገመውም፡፡ ለእርሱም ከባድ ቅጣትን አዘጋጀ፡፡»

**= በንብረት ላይ ሰላም**

وَلَا تَأْكُلُوا أَمْوَالَكُم بَيْنَكُم بِالْبَاطِلِ وَتُدْلُوا بِهَا إِلَى الْحُكَّامِ لِتَأْكُلُوا فَرِيقًا مِّنْ أَمْوَالِ النَّاسِ بِالْإِثْمِ وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ [٢:١٨٨]

«ገንዘቦቻችሁንም በመካከላችሁ በከንቱ (ያለ አግባብ) አትብሉ፡፡ እናንተም የምታውቁ ስትኾኑ ከሰዎች ገንዘቦች ከፊልን በኃጢኣት ትበሉ ዘንድ ወደ ዳኞች አትጣሏት፡፡»

**= የክብር ሰላም**

وَلَا تَقْرَبُوا الزِّنَا ۖ إِنَّهُ كَانَ فَاحِشَةً وَسَاءَ سَبِيلًا [١٧:٣٢]

«ዝሙትንም አትቅረቡ፡፡ እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና፡፡ መንገድነቱም ከፋ!>>

= የአዕምሮ ሰላም፦ በአደንዛዥ ዕጽ በመጠጥ ሰላም አይገኝም

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنَّمَا الْخَمْرُ وَالْمَيْسِرُ وَالْأَنصَابُ وَالْأَزْلَامُ رِجْسٌ مِّنْ عَمَلِ الشَّيْطَانِ فَاجْتَنِبُوهُ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ [٥:٩٠]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው፡፡ (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና፡፡»

፨ ***መብት መስጠት*** ኢስላም በፍጥረታት ምህል ባጠቃላይ በተለያዩ ደራዎች መብቶችን አጽድቋል፡፡ አብሮ ለመኖር መቀራረብ እንዲኖር ሐይማኖታዊ ጥቅሞች አለማዊ ጉዳዮች ቦታ እንዲኖራቸው መብት ያስፈልጋል ይህም በሁለት ይከፈላል፡፡

1-ልዩ የሆነ መብት ፦

وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا ۖ وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا وَبِذِي الْقُرْبَىٰ وَالْيَتَامَىٰ وَالْمَسَاكِينِ وَالْجَارِ ذِي الْقُرْبَىٰ وَالْجَارِ الْجُنُبِ وَالصَّاحِبِ بِالْجَنبِ وَابْنِ السَّبِيلِ وَمَا مَلَكَتْ أَيْمَانُكُمْ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ مَن كَانَ مُخْتَالًا فَخُورًا [٤:٣٦]

«አላህንም ተገዙ፡፡ በእርሱም ምንንም አታጋሩ፡፡ በወላጆችና በቅርብ ዝምድና ባለቤትም፣ በየቲሞችም፣ በምስኪኖችም፣ በቅርብ ጎረቤትም፣ በሩቅ ጎረቤትም፣ በጎን ባልደረባም፣ በመንገደኛም፣ እጆቻችሁም ንብረት ባደረጓቸው (ባሮች)፣ መልካምን (ሥሩ)፤ አላህ ኩራተኛ ጉረኛ የኾነን ሰው አይወድም፡፡»

**2-አጠቃላይ የሆነ መብት ፦**

የአላህ መልእካተኛ (ሰ.ዐ.ወ)-«አትመቀኛኙ አትጨራረቱ አትናቆሩ አት፟ሂ፟ሂሩ ከፊላችሁ ከከፊላቸሁ ሽያጭ ላይ አይሽጥ የአላህ ባሮች ሆይ ወንድማማቾች ሁኑ ሙስሊም ለሙስሊም ወንድሙ ነው፡፡ አይበድለውም አይንቀውም ችላም አይለውም »ወደ ደረታቸው ሶስት ግዜ እያመላከቱ«ተቅዋ እዚህ ቀልብ ውስጥ ነው፡፡ አንድሙስሊምወንድመን በንቀት አይን መመልከት ብቻ ከመጥፎ አድራጎት በቂው ነው፡፡ አንድ ሙስሊም በሌላ ሙስሊም ላይ ደሙም ገንዘቡም ክብሩም ሀራም ናቸው፡፡»

**፨ የአላህ (ሱ.ወ) እዝነት ፍጥረታትን ማዳረስ እኚህም እዝነቶች፦**

**1-የሰው ጅ እዝነት**

የአለህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉ ለአዛኞች አላህ ያዝንላቹሀል መሬት ላይ ላሉት እዘኑ በሰማይ ይታዘንላቹሀል ዝምድናን_ የቀጠላት ይቀጠላል የቆረጣት አላህ ይቆርጠዋል፡፡

**2-ለእንስሳ ማዘን፦** ለወንጀል ምህረት እና ጀነት ለመግባት ለመግባት ምክንያት ተደርጓል

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)አንድሰው በጉዞ ላይ ዕያለ ጥም ያቃጥለዋል ፡፡ የውሀ ጉድጓድ አከኘና ከውስጡ ገብቶ ጠጣ፡፡ ከጉድጓዱ ሲወጣ የሚያለከልክ ውሻ ተመለከተ፡፡ ከደረሰበት ከውሀ ጥም የተነሳ እርጥብ አፈር ይልሳል፡፡ «እኔን የገጠመኝ አይነት የውሀ ጥም ይህንን ውሻ አጋጥሞታል» በማለት አሰበ፡፡ ወደ ጉድጓዱ በመውረድ ጫማውን ውሀ ሞላው፡፡ በአፉ ይዞ ወደላይ ዘለቀ፡፡ ለውሻውም አጠጣው አላህም ይህን

መልካም ስራ ተቀበለው፡፡ «መምህረትንም አደረገለት»በማት ተናገሩ፡፡«የአላህመልእክተኛ ሆይ ለእንስሳ ጽድቅ በመፈጸምምንዳ እናገኛለን?» ሲሉ ጠየቁዋቸው «እርጥብ በሆነች ሆድ ሁሉ ምንዳ ይገኛል፡፡

**፨ ምክክር በዲናዊም በአለማዊ ውስጣዊም ውጫዊም ጉዳይ ታዘናል፡፡**

فَبِمَا رَحْمَةٍ مِّنَ اللَّهِ لِنتَ لَهُمْ ۖ وَلَوْ كُنتَ فَظًّا غَلِيظَ الْقَلْبِ لَانفَضُّوا مِنْ حَوْلِكَ ۖ فَاعْفُ عَنْهُمْ وَاسْتَغْفِرْ لَهُمْ وَشَاوِرْهُمْ فِي الْأَمْرِ ۖ فَإِذَا عَزَمْتَ فَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ ۚ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُتَوَكِّلِينَ [٣:١٥٩]

«ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብክላቸው፡፡ ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በኾንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡፡ ከእነርሱም ይቅር በል፡፡ ለእነርሱም ምሕረትን ለምንላቸው፡፡ በነገሩም ሁሉ አማክራቸው፡፡ ቁርጥ ሐሳብም ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ፡፡ አላህ በርሱ ላይ ተመኪዎችን ይወዳልና፡፡»

፨ እኩልነት፦ በሰው ልጆች ባጠቃላይ ወንዱ ሴት ፤ ነጭ ጥቁር ፤ አረቡ አረብ ያልሆነውም ባጠቃላይ በመሀከላቸው ምንም ልዩነት የለም አላህን በመፍራት ቢሆን እንጂ ሁሉም እኩል ነው፡፡

يَا أَيُّهَا النَّاسُ اتَّقُوا رَبَّكُمُ الَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَاحِدَةٍ وَخَلَقَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَبَثَّ مِنْهُمَا رِجَالًا كَثِيرًا وَنِسَاءً ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ الَّذِي تَسَاءَلُونَ بِهِ وَالْأَرْحَامَ ۚ إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلَيْكُمْ رَقِيبًا [٤:١]«እናንተ ሰዎች

ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአዳም) የፈጠራችሁን ከእርስዋም መቀናጀዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን ከእነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶች የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ፡፡ ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ፡፡ አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና፡፡»

፨ **ፍትህ** ፦ በፍጥረታት ባአጠቃላይ ፍትሐዊ መሆን

إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُ بِالْعَدْلِ وَالْإِحْسَانِ وَإِيتَاءِ ذِي الْقُرْبَىٰ وَيَنْهَىٰ عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ وَالْبَغْيِ ۚ يَعِظُكُمْ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ [١٦:٩٠]

«አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፡፡ ከአስከፊም (ከማመንዘር)፣ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል፡፡ ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል፡፡»

፨ ደሕንነት  በየትኛውም ቦታ በውስጣዊም ውጫዊም ለነገሮች ደህንነት መሰረት መሆን

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት «አዋጅ አልነግራቸሁም ስለሙዕሚን ማን እንደሆን ሰዎች በገንዘባቸው በነፍሳቸው የመኑት ነው ሙስሊም ማለት በምላሱ በእጁ  ሰላም የሆነ ነፍሱን በአላህ መንገድ ላይ የታገለ ማለት ነው ከጥፋት ከወንጀል የተሰደደ ነው፡፡»

፨ **ማነሳሳት፦** በመልካም ስነ-መግባር እና በስራ ላይ ማነሰስ፡-

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት «ከናንተ አንዳችሁ ሰዎች ሰጡትም አልሰጡትም ከሚለምን ገመድ ይዞ ወደጋራ ወጥቶና እስር እንጨት ሰባስቦ በጀርባው በመሸከም እርሱዋን ሸጦ አላህ ፊቱን ቢየብቅለት የተሸለና በላጭ ነው፡፡»

፨ <u>**ንጽህና መማር ማዘዝ ይህም ከተወሱ መልካም ስነ-ምግባር መሐል ይገኝበታል**</u>

- <u>**ከምግብ በፊትም በኃላ እጅን መታጠብ**</u>
- የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት «የምግብ በረካው ከምግብ በፊትና በኃላ ውዱእ ማረግ ነው፡፡»
- <u>**ከምግብ በኃላ አፍን ማጽዳት**</u>

የአላህ መልእክተኛ እንዳስተላለፉት «ምግብ ሚበላ በምላሱ አላምጦ ይዋጥ የቀረውን አፉን ተግሞጥሙጦ የትፋ ይህን የሰራ መልካም ሰራ ያልሰራ ስህተት የለውም፡፡»

- <u>**አፍን በመፋቂ ቦታ ሰጥቶ ማጽዳትን ማነሳሳት**</u>

የአላህ መልእክተኛ እንዳስተላለፉት «ኡመቴን ይቸግረዋል ብዬ እንጂ በሁሉም ሰላት ላይ እንዲፍቁ አዛቸው ነበር»

- <u>**በአካሉ እነዲሁም በሰውነቱ ልብሱላይ ያለውን ቆሻሻ ማስወገድ፡፡**</u>

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት ተፈጥሮ ማለት አምስት ናቸው፡፡ ግርዛት  የብልት ጸጉር ማስወገድ የብብቻን ጸጉር መንጨት ቀድሞ ቀመስን መቀነስ ጥፍርን መቁረጥ ፡፡

**ሁሉት የመጸዳጃ ቦታዎችን ማጽዳት** :

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት ነበዩ (ሰ.ዐ.ወ) «በሽንትም በሰገራም ውደቂብላ እነዳንቅጣጩ በቀኝ እጃችን አንነጸዳዳ ከሶስት ባነሰ ድንጋይ እንዳንጠቀም በፍግ ወይም ባጥንት እንዳንስተናጅ ከልክለውናል፡፡»

**አቅም ያለው ቆንጆ የሆነ ጥሩ ጠረን ያለው ልብስ ይልበስ**

يَا بَنِي آدَمَ خُذُوا زِينَتَكُمْ عِندَ كُلِّ مَسْجِدٍ

‹‹የአዳም ልጆች ሆይ! (ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን) ጌጦቻችሁን በመስገጃው ሁሉ ዘንድ ያዙ፡፡››

⁘ **<u>አምልኮ በሚያረግበት ሰአት ውስጣዊም ውጫዊም ንጽሕና ያስፈልገዋል፡፡</u>**

አካላዊ ንጽሕና ሙስሊም የሆነ ግለሰብ በአምልኮ ሰዐት በቀን 5 ግዜ በሚሰግድበት ሰአት አካሉ ከነጃሳ ቆሻሻ ማንጻት ውዱእ ማድረግ ግዴታው ነው፡፡

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት‹‹ያለጡሀራ ሰላት ተቀባይ አይሆንም የተሰረቀ ለምጽዋት አይበቃም››

- **<u>የዘር ፈሳሽ ካፈሰሰ መታጠብ ግዴታ ነው፡፡</u>**

وَإِن كُنتُمْ جُنُبًا فَاطَّهَّرُوا ۚ

<<(ሴት ጋር በመገናኘት ወይም በሌላ ምክንያት «ጀናባ») ብትኾኑ (ገላችሁን) ታጠቡ››

-ሱናነታቸው የጠነከረ ትጥበት በጁምዐ ሰላት በኢድ ሰላት በሐጅ እና ኡምራ.......... ወዘተ በነዚህ አምልኮ ላይ ገላን መተጣጠብ ተመራጭ አምልኮ ስርአት ነው፡፡

**2 <u>መንፈሳዊ ንጽሕና ነፍስን ሌላን አካል አላህ ላይ ከማጋራት ማጽዳት.</u>**

وَاعْبُدُوا اللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا ۖ

<<አላህንም ተገዙ፡፡ በእርሱም ምንንም አታጋሩ፡፡››

**-ከዩልኝ ስራ ነፍስን ማጽዳት**

وَلَا يَحُضُّ عَلَىٰ طَعَامِ الْمِسْكِينِ [١٠٧:٣]

‹‹ወዮላቸው ለሰጋጆች፡፡››

الَّذِينَ هُمْ عَن صَلَاتِهِمْ سَاهُونَ [١٠٧:٥]

‹‹ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለኾኑት፤ (ሰጋጆች)፡፡››

الَّذِينَ هُمْ يُرَاءُونَ [١٠٧:٦]

<<ለእነዚያ እነርሱ ይዩልኝ ባዮች ለኾኑት፡፡»

وَيَمْنَعُونَ الْمَاعُونَ [١٠٧:٧]

«የዕቃ ትውስትንም (ሰዎችን) የሚከለክሉ ለኾኑት (ወዮላቸው)፡፡»

- **<u>በራስ መደነቅ</u>**

وَلَا تُصَعِّرْ خَدَّكَ لِلنَّاسِ وَلَا تَمْشِ فِي الْأَرْضِ مَرَحًا ۖ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتَالٍ فَخُورٍ

[٣١:١٨]

«ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዟዙር፡፡ በምድርም ላይ ተንበጥርረህ አትኺድ፡፡ አላህ ተንበጥራሪን ጉረኛን ሁሉ አይወድምና፡፡»

- **<u>ምቀኝነት</u>**

  የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል« ምቀኝነትን ተጠንቀቁ እሳት እንጨትን እንደምትበላው ምቀኝነትም መልካም ስራዎችን ይበላል፡፡»

- **<u>ኩራት</u>**

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል «ቀልቡ ውስጥ ቅንጣት ታክል ኩራት ያለበት ሰው ጀነት አይገባም በማለት ተናገሩ» ሰውየውም «ልብሱና ጫማውን መልካም እንዲሆን ይፈልጋል ይህ ከኩራት ይቆጠራልን በማለት አንድሰው ጠየቃቸው፡፡» እርሳቸውም «አላህ ውብ ነው፡፡ ውበትን ይወዳል ኩራት ማለት ሀቅን አለመቀበልና ሰዎችን ዝቅ አርጎ መመልከት ነው፡፡»

## 14 <u>ስነ-ምግባር ፦የኢስላም ተልኮ በሰዎች መካከል የኮደሉ መልካብ እሴቶችን</u> መሙላት ነው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት «እኔ የተላኩት መልካም ባህሪን ላጸድቅ ጥሩ ስነ-ምግባር ልሞላ ነው፡፡»

በመልካም ቢያዘን ቢያነሳሳን ከአጸያፊ ስነ-ምግባር ቢያቅበን ከማህበረሰቡ ጋር ከሌላም ፍጥረታት ጋር ለሚኖረን ግኑንነት ኢስላም ምቹ የሆነ ነው።

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት ክልክል ነገርን ተጠንቅ ከሰዎች መሐል መንገድ በትክክል ጌታህን ተገዚ አላህ ላንተ በመረጠልህ ተጓዝ ከሰወች የተብቃቃህ ትሆናለህ ለጎሮቤትህ መልካም ዋል ሙዕሚን ትሆናለህ ለራስህ የወደድከውን ለሰዎች ውደድ ሙስሊም ትሆናለህ ሳቅ አታብዛ ቀልብህ ይሞታል።

## በሰዎች ላይ መልካምነትን ካፋትን በማራቅ መልካምነትን ማረጋገጥ።

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት «ዕውነተኛ ደሀ ማን እንደሆነ ታውቃለቸሁን» በማለት ተከታዮቻቸውን ጠየቃቸው «ድሀ ማለት እኛ ዘንዳ ዲር ሐምም ሆነ ቁሳዊ ሀብት የሌለው ነው አላቸው» «ተከታዮቼ መሀል ድሀ ማለት የቂያማ እለት በሰላት በጾሞቹና በዘካ ያከማቸውን ምንዳ ይዞ የሚመጣ ነው በዚህች አለም ውስጥ የሰደበ ስሙን ያጎደፈው ገንዘቡን የበላው ያለአግባብ ደሙን ያፈሰሰ ሌላኛውን የመታ ሆኖ ይመጣል ለዚህኛውም በጎ ተግባራት በመፈጸም ያከማቸውን መንዳ ይሰጠዋል ለሌላውም እንዲሁ ከሐሰናው ሰጠዋል ሌሎችን በመበደል የተቆለብ እዳ ከመገባደዱ በፊት ሐሰናው ተማጦ ካለቀ የተበዳዮ ቹን ሀጥያት እንዲሸከም ይደረጋል ከዚያም እሳትውስጥ ይጣላል»አሉ፡፡

ኢስላም በተወሰነ መንገድ የተሳሰረ እና እዝነት ላይ የቆመ ከጥቅም ፍቅር ሚያስቀድም አዲስ ማህበረሰብ መፍጠር የሁልግዜ እቅዱ ነው።ከአላህ ከነብያት ከሰው ልጅ ባጠቃላይ መልካም ባህሪ ስነ-ስርአት ያለው ግኑኝነት እንዲሆን የኢስላም ሙሉ ገጽታ ነው።

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا يَسْخَرْ قَوْمٌ مِّن قَوْمٍ عَسَىٰ أَن يَكُونُوا خَيْرًا مِّنْهُمْ وَلَا نِسَاءٌ مِّن نِّسَاءٍ عَسَىٰ أَن يَكُنَّ خَيْرًا مِّنْهُنَّ ۖ وَلَا تَلْمِزُوا أَنفُسَكُمْ وَلَا تَنَابَزُوا بِالْأَلْقَابِ ۖ بِئْسَ الِاسْمُ الْفُسُوقُ بَعْدَ الْإِيمَانِ ۚ وَمَن لَّمْ يَتُبْ فَأُولَٰئِكَ هُمُ الظَّالِمُونَ [٤٩:١١]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፡፡ ከእነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፡፡ ነፍሶቻችሁንም አታነውሩ፡፡ በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ፡፡ ከእምነት በኋላ የማመጽ ስም ከፋ፡፡ ያልተጸጸተም ሰው እነዚያ እነርሱ በዳዮቹ ናቸው፡፡»

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اجْتَنِبُوا كَثِيرًا مِّنَ الظَّنِّ إِنَّ بَعْضَ الظَّنِّ إِثْمٌ ۖ وَلَا تَجَسَّسُوا وَلَا يَغْتَب بَّعْضُكُم بَعْضًا ۚ أَيُحِبُّ أَحَدُكُمْ أَن يَأْكُلَ لَحْمَ أَخِيهِ مَيْتًا فَكَرِهْتُمُوهُ ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ ۚ إِنَّ اللَّهَ تَوَّابٌ رَّحِيمٌ [٤٩:١٢]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ፤ ከጥርጣሬ ከፊሉ ኃጢአት ነውና፡፡ ነውርንም አትከታተሉ፡፡ ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ፡፡ አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ኾኖ ሊበላው ይወዳልን? (መብላቱን) ጠላችሁትም፤ (ሐሜቱንም ጥሉት)፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ አላህ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡»

**<u>የኢስላም መልእክት በሰዎች እና በጌታቸው መሀል ያለ አደራ ነው፡፡</u>**

إِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُكُمْ أَن تُؤَدُّوا الْأَمَانَاتِ إِلَىٰ أَهْلِهَا وَإِذَا حَكَمْتُم بَيْنَ النَّاسِ أَن تَحْكُمُوا بِالْعَدْلِ ۚ إِنَّ اللَّهَ نِعِمَّا يَعِظُكُم بِهِ ۗ إِنَّ اللَّهَ كَانَ سَمِيعًا بَصِيرًا [٤:٥٨]

«አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱ ያዛችኋል፡፡ በሰዎችም መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ በትክክል እንድትፈርዱ (ያዛችኋል)፡፡ አላህ በርሱ የሚገሥጻችሁ ነገር ምን ያምር! አላህ ሰሚ ተመልካች ነው፡፡»

**<u>ኢስላም እውነተኛ ሐይማኖት ነው፡፡</u>**

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اتَّقُوا اللَّهَ وَكُونُوا مَعَ الصَّادِقِينَ [٩:١١٩]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ከእውነተኞቹም ጋር ኹኑ፡፡»

**<u>ኢስላም የታማኝነት ሐይማኖት ነው፡፡</u>**

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَوْفُوا بِالْعُقُودِ ۚ أُحِلَّتْ لَكُم بَهِيمَةُ الْأَنْعَامِ إِلَّا مَا يُتْلَىٰ عَلَيْكُمْ غَيْرَ مُحِلِّي الصَّيْدِ وَأَنتُمْ حُرُمٌ ۗ إِنَّ اللَّهَ يَحْكُمُ مَا يُرِيدُ [٥:١]

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በቃል ኪዳኖች ሙሉ፡፡ በእናንተ ላይ የሚነበበው ብቻ ሲቀር፡፡ የግመል፣ የከብት፣ የበግና የፍየል እንስሳዎች እናንተ በሐጅ ሥራ ላይ ኾናችሁ ማደንን የተፈቀደ ሳታደረጉ ለእናንተ ተፈቀዱ፡፡ አላህ የሚሻውን ይፈርዳል፡፡»

**ኢስላም ለዘብተኛ እና የእዝነት ሐይማኖት ነው፡፡**

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳስተላለፉት «በአንዳንድ ነገር ማዘን አይገኝም አላህ የለገሰው ቢሆን እንጂ፡ ፡አንድ ነገር ላይ እዝነት አይወገድም ያነወረው ቢሆን እንጂ»

**ኢስላም የፍቅር ሐይማኖት ነው፡፡**

የአላህ መልክተኛ እንዲህ ብለዋል «አንዳችሁም አላምናችሁም ለራሱ ሚወደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ ፡፡»

**<u>የኢስላምን ህግጋት ይዞታ የቀሩትን ስነ-ምግባር በማህበረሰብ በማስረጽ በማዳረስ ከምንጠየቅባቸው ነገሮች መሀል፦</u>**

1- **በመልካም ማዘዝ ከአጸያፊ ተግባራት መከልከል ማቀብ**

كُنتُمْ خَيْرَ أُمَّةٍ أُخْرِجَتْ لِلنَّاسِ تَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَتَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنكَرِ وَتُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ ۗ وَلَوْ آمَنَ أَهْلُ الْكِتَابِ لَكَانَ خَيْرًا لَّهُم ۚ مِّنْهُمُ الْمُؤْمِنُونَ وَأَكْثَرُهُمُ الْفَاسِقُونَ [٣:١١٠]

« ለሰዎች ከተገለጻች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ኾናችሁ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ፤ ከመጥፎም ነገር ታዛላችሁ፤ በአላህም (አንድነት) ታምናላችሁ፡፡ የመጽሐፉም ሰዎች ባመኑ ኖሮ ለነርሱ የተሻለ በኾነ ነበር፡፡ ከነርሱ አማኞች አሉ፡፡ አብዛኞቻቸው ግን አመጸኞች ናቸው፡፡»

2 -**ትክክለኛ በሆነ ውይይት መመካከር ሀሳብ መለዋወጥ**

وَالْعَصْرِ [١٠٣:١]

«በጊዜያቱ እምላለሁ፡፡»

إِنَّ الْإِنسَانَ لَفِي خُسْرٍ [١٠٣:٢]

<<ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው፡፡»

إِلَّا الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ وَتَوَاصَوْا بِالْحَقِّ وَتَوَاصَوْا بِالصَّبْرِ [١٠٣:٣]

«እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ፡፡»

**የተከበሩ አንባቢያን**

ኢስላም መሆን በራሱ ከአላህ የተሰጠ ስጦታ ነው፡፡ ማንም በኢስላም ሊጠቀም አይችልም፡፡ አላህ ያደለው ሲቀር ከታደሉት ለመሆን የግል ጥረት ስለሚያሻው ጥረት ማረግ ይፈልጋል፡፡ በተሰጠህም እድል ለመጠቀም እውነተኛ ተከታይ ለመሆን መጣር፡፡ ይህም ከአላህ ውጭ ያለን ብትገዛ የማይቀበል የሆነው ሐይማኖት ለመሆን ትግል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ኢስላምን ለግል ተቀብሎ መጠቀም በቂ አይደለም እንደውም ወደኢስላም ጥሪ የማድረግ ግዴታ አለብን፡፡ ይህ ኢስላም ያልደረሰበት እንዲሁም ትክክለኛ መረጃ ለሌላቸው አካላት ማድረስ ማብራራት ኢስላም ደርሶት በተቀበለ ሁሉ ግዴታ ሆኗል፡፡

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል «ከኔ የሰማችሁትን አንድም ቃል አድርሱ(አስተላልፉ)»

ይህን መጽሐህ ያዘጋጀሁበት አላማ የኢስላምን ልዩ ገጽታ በተወሰነ መልኩ በማሳየት ትክክለኛ በሆነ በሰዋዊ ተፈጥሮ ይህን ዲን ለማስገንዘብ ነው፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ኢስላምን ኃዋላቀር ሰላም አድፈራሽ ሽብርን ወዳጅ አይነት ገጽታና ስዕል በማላበስ ትክክለኛውን የኢስላምን መልእክት ሲያስተላልፉ አንመለከትም፡፡ ስለኢስላም ግንዛቤ የሌላቸው ሙስሊም ያልሆኑ አካላት ኢስላምን በመሸሻቸው እውነታ አላቸው፡፡ የኢስላም ጠላቶች በስመ ሙስሊም ስለእስልምና ምንም ግንዛቤ የሌላቸውን አካላት በመያዝ በኢስላም ከለላ ተጠያቂነት የጎደለውን ተግባራት በመስራት የኢስላምን ስም እያጎደፉት ይገኛል፡፡የመጽሐፉ የተዘጋጀበት አላማ አጥልቶበት የነበረውን መጥፎ ጥላ ለመግፈፍ በማሰብ ነው፡፡ አላህን ምማጸነው አላህ ትክክለኛውን ጎዳና እንዲያሳየን አይናችንን እነዲገልጥልን የጥፋትን መንገድ ለይቶ እንዲያመላክተን እንዲያርቀን አጥብቄ እለምነዋለው፡፡

# ብስራት

ውድ አንባብያን የኢስላም መልካም ነገሩ ሙስሊም ያልነበረ አካል እስላምን ሲቀላቀል ሁለት ምዳዎች አሉት፡፡

1-ረሱልን አምኖ መልእክቱን እውነት በማለቱ፡፡

الَّذِينَ آتَيْنَاهُمُ الْكِتَابَ مِن قَبْلِهِ هُم بِهِ يُؤْمِنُونَ [٢٨:٥٢]

«እነዚያ ከእርሱ በፊት መጽሐፍን የሰጠናቸው እነርሱ በእርሱ ያምናሉ፡፡»

وَإِذَا يُتْلَىٰ عَلَيْهِمْ قَالُوا آمَنَّا بِهِ إِنَّهُ الْحَقُّ مِن رَّبِّنَا إِنَّا كُنَّا مِن قَبْلِهِ مُسْلِمِينَ [٢٨:٥٣]

«በእነሱ ላይ በሚነበብላቸውም ጊዜ «በእርሱ አምነናል፡፡ እርሱ ከጌታችን የኾነ እውነት ነው፡፡ እኛ ከርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን» ይላሉ፡፡»

أُولَٰئِكَ يُؤْتَوْنَ أَجْرَهُم مَّرَّتَيْنِ بِمَا صَبَرُوا وَيَدْرَءُونَ بِالْحَسَنَةِ السَّيِّئَةَ وَمِمَّا رَزَقْنَاهُمْ يُنفِقُونَ

[٢٨:٥٤]

«እነዚያ በመታገሳቸው ዋጋቸውን ሁለት ጊዜ ይሰሰጣሉ፡፡ ክፉውንም ነገር በበጎ ምግባር ይገፈትራሉ፡፡ ከሰጠናቸውም ሲሳይ ይለግሳሉ፡፡»

2-እስላምናን ከመቀላቀላቸው በፊት የነበሩ ወንጀሎች ባጠቃላይ ምህረት ይደረግላቸዋል፡፡

3-ያለፉ ወነጀሎቹ በጠቅላላ ስራ በመልካም ስራ ምንዳ ይቀየርለታል የህን ደግሞ አላህ ለመረጠው ያደለው ጸጋ ነው፡፡

وَالَّذِينَ لَا يَدْعُونَ مَعَ اللَّهِ إِلَٰهًا آخَرَ وَلَا يَقْتُلُونَ النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ وَلَا

يَزْنُونَ ۚ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ يَلْقَ أَثَامًا [٢٥ «እነዚያም ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የማይገዙት፣ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ የማይገድሉት፣ የማያመነዝሩትም ናቸው፡፡ ይህንንም የሚሠራ ሰው ቅጣትን ያገኛል፡፡»

يُضَاعَفْ لَهُ الْعَذَابُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ وَيَخْلُدْ فِيهِ مُهَانًا [٢٥:٦٩]

«በትንሣኤ ቀን ቅጣቱ ለእርሱ ይደራረባል፡፡ በእርሱም ውስጥ የተዋረደ ኾኖ ይኖራል፡፡»

إِلَّا مَن تَابَ وَآمَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَالِحًا فَأُولَٰئِكَ يُبَدِّلُ اللَّهُ سَيِّئَاتِهِمْ حَسَنَاتٍ ۗ وَكَانَ

اللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا [٢٥:٧٠]

«ተጸጽቶ የተመለሰና ያመነ መልካምንም ሥራ የሠራ ሰው ብቻ ሲቀር፡፡ እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለውጣል፡፡ አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው፡፡»

**ጥሩ በሆኑ እድሎች ከመዘናጋት አደራህን፡-**

‹‹ብልጥ ብሎ ማለት ከሞት ቡኃላ ላለው ሀገር የሰራ ነው ፡፡ ደካማ(ሞኝ) ብሎ ማለት ስሜቱን የተከተለ ማለት እና ያለስራ ጀነትን የተመኘ ነው፡፡››

የአላህ እዝነት እና ሰላም በአላህ መልእክተኛ ሙሀመድ (ሰ.አ.ወ) እና በቤተሶቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸው ይሁን ፡፡

**ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡**